

# ቴዎድሮስ አየለ ማን ነው?

በቦስተን ነዋሪ ቀንደኛ የፋሽቱ ደርግ ካድሬ ነው።

በፋሽሽታዊው የደርግ ዘመነ መንግሥት በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ ተክለኃይማኖት ወረዳ ከፍተኛ 3 የሚከተሉትን ሥፍራዎች ያካተተ ከፍተኛ ካድሬ የነበረ ነው።

- የንግድ ሥራ ት/ቤት (አሁን የንግድ ሥራ ኮሌጅ) ፊት ለፊት፥
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፥
- ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል፥
- የአገር አስተዳደር ጽ/ቤት (አሁን የኢሚግሬሽን ጽ/ቤት)
- ጎላ ሚካኤል፥
- አንበጣ መከላከያ፥
- አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ፥
- ሆቴል ዲአፍሪክ፥
- ሜክሲኮ አደባባይ፥
- ዋቢ ሸበሌ ሆቴል፥
- ተክለ ኃይማኖት፥
- በርበሬ ተራ እና
- ሃደሬ ሰፈር

ቴዎድሮስ አየለ የኢትዮጵያ ወጣት ሴቶችን በማሰር ክብረ ንጽህናቸውን የደፈረ፥ አሻፈረኝ ያሉትን ደግሞ በጠራራ ፀሐይ በፀረ አብዮት ስም የረሸነ፥ የግል ኑሮአቸውን ለማሸነፍ በበርበሬ ንግድ ላይ ተሰማርተው የነበሩትን ነጋዴዎች የረሸነና ያስረሸነ አረመኔና ቀንደኛ የኢትዮጵያውያን ጠላት ነው።

ቴዎድሮስ አየለ ዛሬ በቦስተን ከተማ የበግ ለምድ በመልበስ ተሸሽጎ ኖሮ ዛሬ ከመሰሎቹ ከወያኔ ካድሬዎች ጎን ተሰልፎ አግኝተነዋል። እንደ ጲላጦስ ከሁሉም ንጹህ ነኝ በማለት ዛሬ የወያኔ አፈ ቀላጤ ሆኗል። አይ አሜሪካ ስንቱን ጉደኛ ታቅፊሻል!!!???

አንድነት ኃይል ነው! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ወዳጆች በቃ እስከ መቼ!!!
ገዳይና ገራፊ የደርግና የወያኔ ካድሬዎችን በጋራ እናጋልጥ!!!
(የሌሎቹም እንደዚሁ ይቀጥላል)

## ወንጀለኞችን እንወቃቸው (ቁጥር 2)

### አምባሳደር ሞገስ ሀብተማርያም

አምባሰደር ሞገስ ሀብተ ማርያም የሚታወቀው የፋሺስቱ ደርግ የደህንነት ወይም የስለላ መስሪያ ቤት የውጭ ክፍል ሀላፊ በመሆን በዚህ ስራው ለጨፍጫፊው ደርግ በጣም ጠቃሚ በመሆኑ እስከ ምክትል ሚስትርነት ደረጃ ደርሶ ኋላም በሳውዲ አረቢያ አምበሳደር ተብሎ ተሹሟል። የአምባሰደርነቱ እንጂ የደህንነቱ ስራው እንዲነሳ የማይፈልገው ሞገስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአሜሪካንን ፍቃድ አግኝቶ ልጆች ጥየቃ በሚል ሽፋን ወደ አሜሪካ መመላስን ተያይዟል።

### ሞገስ ሀብተ ማርያም በሕዝብና በሀገር ላይ ምን ወንጀል ፈፅሟል?

በደህንነት በነበረው ሀላፊነት መሰረት የስልክ ጠለፋ ዋና አዛዥና አዘጋጅ በመሆኑ በሚከተሉት ወቅቶችና ግለስቦች ላይ ጠለፋን አዞ ግደያን አስከትሏል---

- በጄኔራል አማን አንዶም ላይ
- በሻለቃ ሲሳይ ላይ
- በሻለቃ ሞገስና ጓደኞቹ ላይ
- በመፈንቅለ መንግሰት በተከሰሱት ላይ--አንዳንዶቹ በተኙበት ሆስፒታል በአልጋቸው ስር መቅጃ በማስቀመጥ ሳይቀር፤ በተቃዋሚ ግለሰቦች ላይ በሀገርም ውስጥ ሆነ በወጭ ሀገሮች በመሰለል።

መረጃው ለደንባራውና ፋሺስቱ መንግስቱ ቀርቦ በብዙዎች ላይ የግድያ እርምጃ ተወስዷል። ሞገስ በአረመኔው በመወደዱ ምክትል ሚኒስቴርና ኋላም አምበሳደር ተብሎ ተሹሟል። ይህን ግለሰብ በማዳነቅ ሌላው የደርግ ሉሌና በግድያ ወንጀል ተጠያቂ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ መኮንን የፃፈውን ያጤኗል። የተስፋዬን ውድቅና ትርኪ ምርኪ መፅሀፍ በማድነቅ ሞገስ በመፅሀፉ ጀርባ የፃፈለትንምና ይህን ዝባዝንኬ መፅሀፍን “ የወርቅ ማዕድን” ያለውን ማየት ይበቃል። ሞገስ ሀብተ ማርያም በዘመነ ደርግ ኢህዴአ/ ወይም ኢፒዲኤ የተባለውን ድርጅት ተከታዮች አጋልጦ ብዙዎችን ያስረሸነና የአሜሪካኑንም ሲአይኤ ሰላይ አስይዞ ያስቀጠቀጠ ሲሆን ታዲያ ዛሬ አሜሪካ ለምን ከልክሉት የነበረውን ቪዛ ሰጠው?

ወያኔስ በስደት ካለበት ሳውዲ አረቢያ ና ግባ ብሉ እንዴት ፈቀደለት? ይህን ወንጀለኛ በተመለከተስ ሁሉ ዝምታ ምነዋ? በሞገስ አማካይነት የተረሸኑ ዘመዶች ወገኖች የሉንም እንዴ? ወንጀለኞች መንም ሳይፈሩ አሜሪካ ሲንደላቀቁ ለምን በዝምታ እናያለን? ሞገስ ያስገደላቸውንስ መቼ ነው የምንበቀለው? መቼ ነው ይህን ወንጀለኛ የምንከሰውና ለፍርድ ይቅረብ የምንለው? መቼ ነወ ወያኔ ከነፍስ ገዳዮቸ ጋር ያለውን ህብረት የምናጋልጠወና የምናወግዘው?

ይቀጥላል.............ወንጀለኞችን ማጋለጣችን..

ሞገስ ሀብተ ማርያም ፀረ ሕዝብ ውንጀለኛ ነው። ይጋለጥ! ይወገዝ! የምን አምባሳደር ነፍሰ ገዳይ ወንጀለኛ እንጂ!!